ethio telecom™
ኢትዮ ቴሌኮም

www.ethiotelecom.et

P.O. Box 1047 Addis Ababa Ethiopia
tel.: +251 (0) 115 505 678
fax: +251 (0) 115 515 777

ሐምሌ 11 ቀን 2010 ዓ.ም

የወደፊት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠን በመንግስት በኩል አዲስ አገራዊ የኢኮኖሚ ሪፎርም ተግባራዊ ለማድረግ አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡ በተለይም በቴሌኮም ዘርፍ ይህንኑ ተልዕኮ በአዲስ ሃይል ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በተቋሙ ቀደም ሲል የነበረው የሥራ አመራር ቦርድ እና የዋና ሥራ አስፈፃሚ ለውጥ ተደርጓል፡፡

ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ዘርፉ የራሱን የላቀ ድርሻ እንዲያበረክት በሚጠበቀው ተቋም ቀደም ሲል በሥራ አመራር ቦርድ እንዲሁም በዋና ሥራ አስፈፃሚ ለተመዘገቡ ውጤቶች ጠንካራ አመራር ሲሰጡ የነበሩ የሥራ ሃላፊዎችን በክብር ለመሸኘትና አዲስ የተመደቡት የሥራ አመራር ቦርድ አባላት እና የዋና ሥራ አስፈፃሚ የእንኳን ደህና መጣችሁ የአቀባበል ኘሮግራም ተዘጋጅቷል፡፡

የቀድሞው የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶ/ር አንዱዓለም አድማሴ ቀደም ሲል ተቋሙን ወደ አዲስ አደረጃጀት ለማሸጋገር በተደረገው ተግባር ከትራንስፎርሜሽኑ ጀምሮ አሁን ለደረሰበት የዕድገት ደረጃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፣ ለዚህም አስተዋፅኦአቸው ተቋሙ እጅግ እያመሰገነ በቀጣይም አዲስ በተሾሙበት የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር መልካም የስራ ዘመን እንዲሆንላቸዉ ከልብ ይመኛል ፡፡

Ethio telecom Head Office
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Shared Reflection!

ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም
www.ethiotelecom.et
P.O. Box 1047 Addis Ababa Ethiopia
tel.: +251 (0) 115 505 678
fax: +251 (0) 115 515 777

በመሆኑም፣ ይህን አዲሱን አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል ክብርት ወ/ሪት ፍሬህይወት ታምሩ ከሐምሌ 16 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የቀድሞውን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶ/ር አንዱዓለም አድማሴን በመተካት የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ስራ አስፈፃሚ ሆነው ተሾመዋል፡፡

ክብርት ወ/ሪት ፍሬህይወት ታምሩ ከኦፕን ዩኒቨርስቲ /United Kingdom/ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ማስተርስ ዲግሪ /MBA/ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢንፎርሜሽን ሲስተም የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን በቴሌኮም ዘርፉም ለ8 ዓመታት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፉን በመምራት ጨምሮ እስከ ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚነት ድረሰ አገልግለዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም የኢትዮ ቴሌኮም የሥራ አመራር ቦርድ አባል፣ በግል ዘርፉ የዶክሳ አይቲ ቴክኖሎጂ ኩባንያ መስራችና ማኔጂንግ ዳይሬክተር እንዲሁም የተለያዩ ፈርቀዳጅ የሆኑ አዳዲስ ጀማሪ ኩባንያዎችን (Startup Campiness Establishment and Implementation) በማቋቋም እና ወደ ተግባር በማስገባት በማገልገል ላይ ነበሩ፡፡

Ethio telecom Head Office
Federal Democratic Republic of Ethiopia
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮ ቴሌኮም ዋናው መ/ቤት

Shared Reflection!